# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 188 ታህሳስ 12 2004 ገጽ 1

የኢትዮጵያን ፓለቲካና ኢኮኖሚ ተቆጣጥረው የድሆችን ደም እየመጡ ያሉት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላትና ሎሌዎች እአአ ከ1990 መጀመሪያ እስከ 2007 መጨረሻ በነበሩት 18 ዓመታት ውስጥ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ ማሸሻቸው የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) በጥናት ማረጋገጡን ይፋ ካደረገ አንድ ዓመት አልሞላውም።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የሠራዊቱን የብሔር ተዋጽኦ ለማመጣጠን የምልመላ መስፈርቶች ዝቅ እንዲል ተደርጎአል ሲል የወያኔው የመከላከያ ሚኒስቴር ገለጸ

በህወሃት የበላይነት በሚመራው የአገሪቱ መከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ያለው የአዛዥነት ቦታ ሙሉ በሙሉ ለማለት በሚያስደፍር መልኩ ከትግራይ ብሄር በመጡ ኀጠኞች መያዙን የግንቦት 7 ንቅናቄ ካጋለጠ ወዲህ፤ የብሄረሰብ ተዋጾ ለማመጣጠን በሚል የተለያዩ የማስመሰያ ጥገናዊ ለውጦች ሲነገሩ የቆዩ ቢሆንም ሲራጅ ፋጌሳ በተባለው የይስሙላ መከላኪያ ምንስትር ባለፈው ማክሰኞ ለወያኔ ፓርላማ የቀረበው የዘር ተዋጽኦ ሪፖርት በርካታ የአገሪቱን ፖለቲከኞች ያሳቀ ሆኖ መገኘቱን ዘጋቢያችን ከአድስ አበባ በላከው ሪፖርት ገለጸ።

በደደቢት በረሃ ተደራጅተው ለስልጣን የበቁት የህወሃት መሪዎች አብሮአቸው የታገለውን የህወሃት ታጋይ በሙሉ ከፍተኛ የመደበኛ ትምህርትና ወታደራዊ ሳይንስ ሥልጠና በሚጠይቁ ወታደራዊ መኮንነት ቦታዎች ሁሉ ላይ ከመቶአለቅነት እስከ ጀነራልነት ማዕረጎች በመሾም ሌሎች የአገሪቱ ተወላጆች በገዛ አገራቸው ባይተዋርነት እስኪሰማቸው ድረስ በበታቸኝነት ስሜት እንዲሸማቀቁ እየተደረገ ለተራ ወታደርነት የሥራ መደብ ስለ ብሄረሰብ ተዋጾ ማውራት የሚጠቅመው ነገር እንደሌለ ብዙዎች ይስማማሉ።

ገና 11 ኛ ክፍል ተማሪ በነበረበት ወቅት በረሃ የገባውና ወያኔን ትግል የተቀላቀለው ሳሞራ ዩኑስ በብሄራዊ ሙዚዬም ውስጥ የመታሰቢያ ሃውልት የቆመለትና በአገሪቱ የመጀመሪያው ባለሙሉ ጀነራል ማዕረግ ተሿሚ እንደሆነ ሲታወቅ እርሱ በበላይነት በሚያሽከረክረ የመከላኪያ ምንስትር ውስጥ ለብሄረሰብ ተዋጾ አስረጅነት ሲባል ለይስሙላ ከኦሮሞ ብሄረሰብ በምንስትርነት ማዕረግ የተሾመው ሲራጅ ፈጌሳ ሳሞራ ዩኑስ በማያውቅ ምንም ነገር የመወሰን መብት እንደሌለው ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የህወሀት ጄኔራሎችና ኩባንያቸው ኢፈርት በጦር መሳሪያ ሺያጭ ውስጥ እንደተዘፈቁና በጎሬቤት አገር ዘረፋ እያካሄዱ መሆኑ ተዘገበ

ድርጅታቸው ህወሃትን ለድል በማብቃታቸው ለጄኔራልነት ማዕረግ የበቁት የቀድሞ "የትግራይ ታጋዮችና" የንግድ ድርጅታቸው ኢፈርት በአገር ውስጥ የሚያካሂዱትን ዘረፋ አድማስ በማስፋት ከሁለት አስርተ አመታት በላይ በጦርነት እየተታመሰች ካለቺው ጎሬቤት አገር ሱማሊያ ተገንጥላ ካለቺው ፑትላንድና ከአዲስቷ የደቡብ ሱዳን ተለይታ የራሷን አስተዳደር ለመመስረት ትግል የጀመረቺውን የጁባ አማጽያን ጋር በመሻረክ ከፍተኛ ጥቅም በሚያስገኝ ዘረፋ ላይ መጠመዳቸውን የኢትዮጵያ ሳታላይት ቴለቪዥን ኢሳት ዘገበ።

ኢሳት ታማኝ ምንጮቹን በመጥቀስ እንደዘገበው፤ የህወሀት ጄኔራሎች ከኢትዮጵያ ህዝብ በተሰበሰበ ግብር የተገዙትንና የመከላከያ ሚኒስቴር ንብረት የሆኑትን የጦር መሳሪያዎች ለፑንትላንድ እና በቅርቡ ነጻነቷን ካወጀቺው ደቡብ ሱዳን ለመገንጠል እየታገሉ ላሉ የጦር መሪዎች በከፍተኛ ደረጃ በመቸበቸብ በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር ሀብት በማጋበስ ላይ ናቸው።

የጦር መሳሪያዎች ሽያጭ የሚከናወነው በጥሬ ገንዘብ እጅ ለእጅ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ከሽያጩ ስለሚገኘው ገንዘብ ምንም መረጃ የለውም።

በአገሪቱ መከላኪያ ከሎጂስቲክስ አቅርቦት እስከ ጦር መሳሪያዎች ግምጃ ቤት ያሉት የሃላፊነት ቦታዎች በሙሉ በህወሀት አባላት የተያዙ በመሆናቸው፣ የኦዲት ስራ ለመስራትና የንብረት ቁጥጥር ለማድረግ አስቻገሪ ሆኗል ያለው የኢሳት ዘገባ፤ በጄኔራልነት ማእረግ የሚጠራው ሳሞራ የኑስ ከአመት በፊት የመከላከያ ወጪ ኦዲት እንዲደረግ ሲጠየቅ "የትኛው ባለስልጣን ነው መከላከያን ኦዲት ሊያደርገው የሚችለው? በማለት ዝቶ እንደነበር መዘገቡን አስታውሶአል።

እንደ ኢሳት ምንጮች መረጃ የህወሀት ጄኔራሎች ለፑንትላንድ እና ለጁባ የጦር አበጋዞች የሚሸጡዋቸው የጦር መሳሪያዎች በአብዛኛው፣ በትከሻ ላይ የሚተኮሱ ላውንቸሮች፣ ክላሽንኮቭ ጠመንጃዎች፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠር ጥይቶች፣ የተለያዩ የእጅ ቦንቦች እና ወታደራዊ ተሽከርካሪዎች ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ በአሁኑ ጊዜ አንድ ክላሽንኮቭ እስከ 12 ሺ ብር በመሸጥ ላይ ነው የሚለው የኢሳት ዘገባ የህወሀት ባለስልጣናት ከሸጡዋቸው በሺዎች የሚቆጥሩ የጦር መሳሪያዎች በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ዶላር እንዳካበቱ መረጃዎች ያመለክታሉ ብሎአል።

የወያኔ ጀኔራሎች በሁለቱ ጎሬቤት አገሮች እያጧጧፉ ያለውን ዘረፋ የዘገበው ኢሳት በፑንትላንድ እና በጁባ ከሚቸበችቡት የጦር መሳሪያዎች በተጨማሪ፣ የህወሀት ኩባንያ የሆነው መስፍን ኢንጂነሪንግ ደግሞ በጦርነቱ ጊዜ በእነዚህ አገሮች የወዳዳቁትን የጦር መሳሪያዎች እና የተለያዩ ብረታ ብረቶች በመሰብሰብ መቀሌ ወደ ሚገኘው ፋብሪካው እያጋዘ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለነጻነት የሚታገሉት አርበኞች ላይ የፈበርከውን የፈጠራ ወንጀል ለማጠናከር የሃሰት ምስክር ሆነው የሚቀርቡት ሁሉ የሚጠየቁበት ቀን እንደሚመጣ ሊያውቁት ይገባል ሲል ግንቦት 7 መግለጫ አወጣ

ግንቦት 7 የፍትህ የነጻነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በሚያቀነባበረው የፈጠራ ወንጀል በገንዘብ ወይም በሌላ ቁሳዊ በረከት ተገዝተው በሃሰት ለመመስከር የተመለመሉና ስልጠና የወሰዱ ሰዎች ሁሉ ታሪክ ይቅር የማይል ወንጀል እየሰሩ መሆናቸውን ሊያውቁ ይገባል ሲል መግለጫ አውጥቶአል።

ዕሁድ ታህሳስ 8 ቀን "**ሃሰተኛ ብርቱ ወንጀለኛ** " በሚል ርዕስ ግንቦት 7 ያወጣው ይህ መግለጫ፤ ለራሳቸው፣ ለአገራቸውና ለወገናቸው ነፃነት ሲሉ የተቃውሞ ድምጽ ባሰሙ ወገኖቻችን ላይ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በህግ ሽፋን የሚያደርሰው በደል በዝቶ ሕዝብ መሸከም ከሚችለው በላይ ሆኗል ካለ ቦኋላ "ወገኖቻችን በዘረኞች መደብደባቸው፣ መሰደባቸውና መዋረዳቸው ሳያንስ ለዘረኞቹ የፈጠራ ክስ ምስክር ለመሆን ቃለ-መሃላ የሚፈጽሙ፤ በፈጣሪ ስም የሚምሉ ሰዎችን ማየት ህሊና ሊታገሰው ከሚችለው በላይ የሚያሳምም ስቃይ ሆኖአል" ብሎአል።

"በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘመን እያንዳንዱ የፍርድ ቤት ውሎ ወደ አሳዛኝ ትያትር መድረክነት መቀየሩ የታወቀ ነው" የሚለው የግንቦት 7 መግለጫ በትያትሩ ውስጥ እየሆነ ያለው ግን የሰውን ሕይወት አደጋ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን እውነት እራሷ አደጋ ላይ ነች ፤ አገር ጭምር አደጋ ላይ ነች በማለት በዚህ ትያትር የሚተውን ሁሉ በሰው ሕይወት፣ በእውነትና በአገር ላይ ተጨባጭ የሆነ አደጋ እየፈጠረ እንደሆነ ይታወቅ ሲል የቲያትሩ ተዋኒያንን አስጠንቅቆአል።

መግለጫው በማያያዝም "ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ ተላላኪዎች በሚያዟቸውና በአሰለጠኗቸው መንገድ በመሃላ እየዋሹ የሚመሰክሩ ሰዎችን መከታተልና መመዝገብ ተገቢ ነው ብሎ ያምናል ። እነሱም ተገቢውን ፍርድ የሚያገኙበት ጊዜ ይመጣል። ለጥቅም ሲሉ በሃሰት ለመመስከር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ማዋረድ፣ መናቅና ማግለል ተገቢ እና ከስነ-ምግባር አኳያ ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው ብሎ ያምናል" ብሏል።

*የግንቦት 7 መግለጫን ሙሉ ቃል በገጽ 2 ቀርቧል።*

## የወያኔ ፍርድ ቤት በሰላም ታጋዮችና ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ላይ የተፈበረከውን የፈጠራ ወነጀል ክስ አስመልክቶ የቀረቡትን የሃሰት ምስክሮች ቃል ሰምቶ እንደጨረሰ ተገለጸ

በዘረኛው መለስ ዜናዊ ቃል የሚመዘወረው የወያኔ ፍርድ ቤት በነ አንዱአለም አራጌና ሌሎች 24 ሰዎች ላይ የተፈበረከውን የፈጠራ ክስ በማስረጃ ለማጠናከር በውሸት እንዲመሰክሩ ስልጠና ወስደው የቀረቡትን 30 ሰዎች ምስክርነት ቃል አድምጦ ሌላ ተጨማሪ የኦዲዮና የቪዲዮ ማስረጃ ለማየት ተለዋጭ ቀጠሮ እንደሰጠ የደረሰን ዜና ገለጸ።

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ ተጀምሮ ማክሰኞ ታህሳስ 10/2004ዓ/ም የተጠናቀቀውን ይህንን የምስክሮች ቃል መስማት የፍርድ ቤት ውሎ የተከታተሉ ምንጮች እንደገለጹት፤ የአሁኑን የወያኔ የፈጠራ ክስ ድህረ ምርጫ 97 ከታየው የሚለየው ምስክሮች የተባሉት ሁሉ በሰጡት ምስክርነት መጸጸታቸውንና አንድ ሃይል ከኋላቸው ሆኖ የሚያስፈራራቸው መሆኑን መደበቅ አለመቻላቸው በግልጽ ይታይባቸው እንደነበረ መስተዋሉ ነው ብለዋል።

ከመሃላ መፈጸም ሥነሥር ዓት እስከ መጨረሻው የምስክርነት ቃል አንገታቸውን ደፍተውና በሃዘን ስሜት ውስጥ ሆነው ምስክርነት ሰጥተዋል የተባሉት አብዛኛዎቹ ምስክሮች ከተከሳሾች ጠበቃ ለቀረበላቸው መስቀለኛ ጥያቄ ይሰጡ የነበረው ምላሽ ቀደም ሲል የሰጡትን ቃል የሚቃረንና ተከሳሾች ጥፋተኛ ናቸው የተባሉበትን ጭብጥ የማያስረዳ በዚህም ምክንያት ዳኞቹ ሳይቀር የተሸማቀቁበት እንደነበረ ተዘግቦአል።

ወያኔ በቅርቡ አክልዳማ በማለት ለህዝብ እይታ ባቀረበው ድራማ ላይ ጥፋተኛ በመባል በቁጥጥር ሥር ዉለዉ በራሳቸውና በሌሎች ተከሳሾች ላይ የጥፋተኝነት ምስክርነት ቃል ሲሰጡ የነበሩት ከእስር ተለቀው የአቃቤ ህግ ማስረጃ በመሆን ፍርድ ቤት እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን ተመልካችን ያስገረመው የምስክርነት ቃላቸውን ከጨረሱ ቦኋላ በፖሊስ መኪና ተጭነው ከግቢው መውጣታቸው ነው።

እስከዛሬ በፍርድ ቤቱ ከቀረበው ክስና ማስረጃ ለመረዳት እንደተቻለው ወያኔ በሽብርተኝነት ክስ የመሰረተባቸው ታጋዮች በሙሉ ባለፈው መስከረም በህጋዊ መንገድ ሰላማዊ ሰልፍ ለመጥራት ፈቃድ ተጠይቆበት በነበረው ሰላማዊ ሰልፍ ላይ በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ተሳትፈዋል የሚል ብቻ እንደሆነ ለመረዳት ተችሎአል።

የፍርድ ውሎውን የተከታተሉ አንድ የውጪ አገር ዜጋ በሰላማዊ መንገድ የተቃውሞ ሰልፍ መጥራት በሽብርተኝነት የሚያስከስስ መሆኑን ማየታቸው ለርሳቸውና ለአገራቸው መንግሥት ስለመለስ ዜናዊ ምንነት ለማወቅ የመጨረሻው ማስረጃ እንደሆናቸው ለዘጋቢያችን በሰጡት አስተያየት ገልጸዋል።

## ዝርፊያም ዘረኝነትም፤ በቃን!!!!

የኢትዮጵያን ፓለቲካና ኢኮኖሚ ተቆጣጥረው የድሆችን ደም እየመጡ ያሉት የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላትና ሎሌዎች እአአ ከ1990 መጀመሪያ እስከ 2007 መጨረሻ በነበሩት 18 ዓመታት ውስጥ 8.3 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ ማሸሻቸው የተባበሩት መንግሥታት የልማት መርሃግብር (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ) በጥናት ማረጋገጡን ይፋ ካደረገ አንድ ዓመት አልሞላውም።

ስምንት ቢሊዮን ሶስት መቶ ሚሊዮን (8.3 ቢሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ማለት ዜናው በተነገረበት ወቅት 150 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነበር። ይህን ያህል መጠን ባለው ገንዘብ ደግሞ 50, 000 የጤና ጣቢያዎችን ወይም 150, 000 አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን መሥራት ይቻል እንደነበር በጊዜው ተወስቷል።

አንድ መቶ አምሳ ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር፣ በወሬው ብቻ የኢትዮጵያን ሕዝብ እያራቆተ ያለውን የአባይ ግድብ ወጪን ሸፍኖ በአዋሽና በተከዜ ወንዞች ላይ ለምግብ የሚሆኑን እህሎችን ለምናመርትበት መስኖ ሥራ የሚያገለግሉን አራት ተጨማሪ መለስተኛ ግድቦችን ይሰራ እንደነበር በወቅቱ ተዘግቧል።

ያኔም ቢሆን "የዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጥናት የተሟላ ላይሆን ይችላል፤ ዘረፋው ከዚህ በላይ ነው" ያሉ ነበሩ። "የዩ.ኤን.ዲ.ፒ ጥናት ባላካተታቸው ቅርቦቹ ዓመታት ዘረፋው በዝቷል" በማለት የተከራከሩ ነበሩ። እነዚህ ሰዎች ትክክል የነበሩ መሆናቸው የሚያረጋግጥ ተጨማሪ መረጃ ሰሞኑን ይፋ ሆኗል።

የዓለም የፋይናንስ ኢንቴግሪቲ (Global Financial Integrity) ባደረገው ጥናት መሠረት እአአ ከ2000 መጀመሪያ እስከ 2009 መጨረሻ ባሉት 10 ዓመታት ውስጥ 11.7 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ከኢትዮጵያ በህገወጥ መንገድ ወጥቶ መቅረቱ አረጋግጧል።

አስራ አንድ ቢሊዮን ሰባት መቶ ሚሊዮን (11.7 ቢሊዮን) የአሜሪካ ዶላር ማለት በአሁኑ ምንዛሪ **202.2** ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው። አገሪቱን ከጫፍ እስከጫፍ በባቡር ለማገናኘት ያስፈልጋል ተብሎ የተነገረን የገንዘብ መጠን 170 ቢሊዮን ብር ነው። የተዘረፈው 202 ቢሊዮን ብር ነው።

እ.አ.አ. በ2009 - በአንድ ዓመት ውስጥ ብቻ - የተዘረፈው መጠን 3.26 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማለትም 56.34 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ነው። ይህ ደግሞ በ2007ም ሆነ በ2008 ከተዘረፈው የገንዘብ መጠን ጋር ሲነፃፀር በእጥፍ ይበልጣል። በ2009 የኢትዮጵያ አጠቃላይ የወጪ ንግድ 2 ቢሊዮን ያህል ነበር። የተዘረፈው ገንዘብ ከአጠቃላዩ የወጪ ንግድ በምን ያህል መጠን እንደሚበልጥ ልብ ይሏል!

የመለስ ዜናዊ ዘረኛና ዘራፊ አገዛዝ እየተደራረቡ የመጡበትን የሙስና ክሶችን ማስተባበል ከማይችልበት ደረጃ ላይ በመድረሱ እያቅማማም ቢሆን ዘረፋ መፈጸሙን አምኖ በሌሎች ላይ ማላከኩን ተያይዞታል። በዚህ ረገድ ምዝበራው እየተደረገ ያለው "በንግዱ ማኅበረሰብ አካላት በተለይም በወጪና ገቢ ንግድ በተሰማሩ ነጋዴዎች በሚቀርቡ የሃሰት ደረሰኞች ነው" የሚል ማደናገሪያ እያቀረበ ነው።

ይህ ማደናገሪያ እውነትነት አለውን?

አዎ። እውነትነት አለው። ደረሰኝ በማምታታት የኢትዮጵያ ሃብት እየተዘረፈ መሆኑ መለስ ዜናዊ ከመናገሩ በፊትም የታወቀ ጉዳይ ነው። ሆኖም ግን እዚህ ላይ ሁለት አበይት ጥያቄዎችን ማንሳት ያስፈልጋል።

1. የአገሪቱ አጠቃላይ የወጪ ንግድ ዋጋ 2 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ሆኖ እያለ ደረሰኝ በማምታታት ብቻ እንደምን "የተጣራ" 3.26 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ማጭበርበር ይቻላል? እንዴት ዓይነት የሂሳብ፣ የጉምሩክ እና የንግድ ሥርዓቶች ናቸው ይህን ዓይነቱን ግዙፍ ምዝበራ "ማየት" የማይችሉት? ወይስ ከንግዱ በተጨማሪ ገንዘብ የሚወጣበት ሌላም መንገድ አለ?
2. በደረሰኝም ሆነ በሌላ መንገድ ለዘረፋ መንገድ የተመቻቸለት ነጋዴ ማነው? የኤፈርት አስራ አምስት፣ የደጀና ኢንዶውመንት ሰባት እንዲሁም በአክሲዮን ሽፋን የተቋቋሙ ሠላሳ በድምሩ አምሳ ሁለት ግዙፍ የወያኔ ኩባንያዎችም "ነጋዴዎች" ተብለው ነው የሚጠሩት?

ቀድሞ የዩ.ኤን.ዲ.ፒ አሁን ደግሞ የዓለም የፋይናንስ ኢንቴግሪቲ ጥናቶች ውጤት ይፋ መደረጋቸው ጠቃሚ ነገር ነው። እነዚህ ሁለት ጥናቶች የመለስ ዜናዊ አገዛዝን ዓይን ያወጣ ዘረፋን ሙሉ በሙሉ ይገልፃሉ ማለት ግን አይደለም። ገና ብዙ መመርመር ያለባቸው ነገሮች አሉ።
እውን ሰነዶች እንደሚያሳዩት፣ ለም መሬታቶቻችን ለቻይናና አረብ ቱጃሮች ለ99 ዓመታት የተሰጣቸው በሄክታር ከ10 ዶላር ባነሰ ሂሳብ ነው፤ ወይስ ቀሪውን በእጅ አዙር የሚቀበል አለ?

1. እስከዛሬ በልማት ርዳታ ስም የገባው ተሰፍሮ የማያልቅ ገንዘብ በምን ሥራ ላይ ዋለ? አሁንስ በምን ላይ እየዋለ ነው? ያ ሁሉ ገንዘብ የምናያቸውን መንገዶች ብቻ ነው የሚሠራው፤ ወይስ እነሱም የተሰሩት "ለአሳይቶ መለመኛነት" ነው?
2. በግድብ ግንባታ ስም ከድሃው የተሰበሰበውና እየተሰበሰበ ያለው ገንዘብ በተመሳሳይ መንገድ ከአገር ላለመውጣቱ ወይም አገር ውስጥ ሆኖም ላለመዝበሩ ምን ማረጋገጫ አለን?
3. በየአመቱ ይኸን ያህል ገንዘብ እያሸሹ ያሉ ሰዎች ከተሞች ውስጥ ሕንፃ የሚገነቡት ድሃውን "እንቁልልጭ" ለማለት ነው፤ ወይስ የድሆች ጎጆዎች በትዕዛዝ ፈርሰው ህንፃዎቻቸውን ለመኖሪያነት በማከራየት ሌላ ዘረፋ ለማካሄድ?
4. ዋነኛው ጥያቄ ደግሞ ይህ ነው። ከዚህ ሁሉ ዝርፊያ ተጠቃሚዎቹ እነማን ናቸው? ምን ያህል ናቸው? ተጎጂዎቹስ እነማን ናቸው? ምን ያህል ናቸው?

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ንብረታችን ሲመዘበር፤ የድሃው አጥንት ሲጋጥ በዝምታ ማለፍ የለብንም ብሎ ያምናል። በተጨማሪም የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዝርፊያን ለዘረኛ ዓላማው ማስፈፀሚያነት እየተጠቀመ ስለሆነ አገዛዙ ሳይወገድ ዝርፊያን ማቆም አይቻልም የሚል እምነት አለው። በአገራችንና በሕዝባችን ላይ እየተፈጸመ ያለው ዝርፊያ ለከት ማጣት ያንገበገበን ሁሉ ትኩረታችን ማረፍ ያለበት የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝን በአስቸኳይ ማስወገድ እና በምትኩ ፍትህ፣ ነፃነትና ዲሞክራሲ የሰፈኑበት ሥርዓት መገንባት ነው ብሎ በጽኑ ያምናል።

ስለሆነም ግንቦት 7 "ዝርፊያ በቃን!!!" ሲል "የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በቃን!!!" ማለቱ ጭምርም እንደሆነ ማስገንዘብ ይወዳል።

**በዘረኛ ዘራፊዎች መገዛት በቃን!!!!**

**በቃ!!! ጋዬ!!! ይአከል!!! አሎኒ!!! ዲታህ!!! ወጣንደም!!! በስ!!! ጊዴስ!!!**

................................................................................................................

## ሃሰተኛ - ብርቱ ወንጀለኛ!!! (ከግንቦት 7 የተሰጠ መግለጫ ታህሳስ 8 2004 )

ስለ ሃሰት - በተለይም በሃሰት ስለመመስከር - አባቶቻችንና እናቶቻችን ያቆዩልን በርካታ ሥነ-ቃሎች አሉን። አንዱ በአርዕስትነት የተጠቀምንበት "ሃሰተኛ፤ ብርቱ ወንጀለኛ!" የሚለው ነው።

ለራሳቸው፣ ለአገራቸውና ለወገናቸው ነፃነት ሲሉ የተቃውሞ ድምጽ ባሰሙ ወገኖቻችን ላይ የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በህግ ሽፋን የሚያደርሰው በደል በዝቶ ሕዝብ መሸከም ከሚችለው በላይ ሆኗል። ወገኖቻችን በዘረኞች መደብደባቸው፣ መሰደባቸውና መዋረዳቸው ሳያንስ ለዘረኞቹ የፈጠራ ክስ ምስክር ለመሆን ቃለ-መሃላ የሚፈጽሙ፤ በፈጣሪ ስም የሚምሉ ሰዎችን ማየት ህሊና ሊታገሰው ከሚችለው በላይ የሚያሳምም ስቃይ ነው።

በመለስ ዜናዊ አገዛዝ ዘመን እያንዳንዱ የፍርድ ቤት ውሎ ወደ አሳዛኝ ትያትር መድረክነት መቀየሩ የታወቀ ነው። በትያትሩ ውስጥ ግን የእውነት እየሆነ ያለ ነገር ግን አለ። የሰው ሕይወት አደጋ ላይ ነው። እውነት አደጋ ላይ ነች። አገር አደጋ ላይ ነች። በዚህ ትያትር የሚተውን ሁሉ በሰው ሕይወት፣ በእውነትና በአገር ላይ ተጨባጭ የሆነ አደጋ እየፈጠረ እንደሆነ ይታወቅ።

የሰውን ሕይወት፣ አገርምና ነፃነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ጨዋታ ሊኖር አይገባም።

የመለስ ዜናዊ ቅጥረኞች ለሚፈጥሯቸው ክሶች ተስማሚ የሆኑ የሃሰት ምስክሮችን ማሰልጠን ራሱን የቻለ ሙያ እየሆነ ነው። "የሃሰት ምስክሮች ሥልጠና" የሥልጠና መርሃ ግብርና የሥልጠና ማንዋል ሳይቀር ተቀርጾለታል፤ በጀት ተመድቦለታል። ልክ እንደ ሙያ ስልጠና ሆቴል ውስጥ በሃሰት መመስከርን በቲዎሪም በተግባርም ተለማምደው ዋሾ መስካሪዎች ይመረቃሉ።

ይህ እጅግ አሳፋሪና አስነዋሪ ድርጊት ማኅበረሰባችን የቆመበትን "ይሉኝታ" የተባለውን የስነ-ምግባር ምሰሶ ንዶታል። "ተመራቂ ዋሾ መስካሪዎች" ያላዩትና ያልሰሙትን ነገር እንዳዩና እንደሰሙ አድርገው በፈጣሪ ስም ምለው ይዋሻሉ።

በውሸት መመስከር ጥቂት ጥቅሞችን ያስገኛል፤ ሆኖም ግን የማያልቅ ፀፀትና ለትውልድ የሚተርፍ ሃፍረትን ያከናንባል። በተለይም ደግሞ በሃሰት ምስክርነት የአምባገነኖች መጠቀሚያ መሆን እና ንጹሃን ዜጎችን ለሰቆቃ መዳረግ ይቅርታ የሌለው ወንጀል ነው።

ሃሰት እያደር ይቀላል። ሃሰተኛም ይቀላል፤ ይዋረዳል። ሃሰተኛ ምስክር በገዛ ራሱ ቤተሰቦች ሳይቀር የተናቀ ይሆናል። ከሁሉም በባሰ ሃሰተኛ ምስክር በገዛ ራሱ ህሊና የተናቀ ሰው ይሆናል።

በአንፃሩ ደግሞ "እውነት የተናገረ በመርከብ የተሻገረ" ይባላል። በእንዲህ ዓይነት ወቅት እውነትን ለመናገር ድፍረት ያገኙ እነሱ ታላላቆች ናቸው። ዛሬ እውነትን በመናገራቸው ጥቃት ይደርስባቸው ይሆናል። ሆኖም በሕዝብ ተከብረው፤ ከህሊናቸው ጋር ታርቀው ኮርተው ይኖራሉ። ቢሞቱም ስማቸው ከመቃብር በላይ ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የመለስ ዜናዊ ተላላኪዎች በሚያዟቸውና በአሰለጠኗቸው መንገድ በመሃላ እየዋሹ የሚመሰክሩ ሰዎችን መከታተልና መመዝገብ ተገቢ ነው ብሎ ያምናል። እነሱም ተገቢውን ፍርድ የሚያገኙበት ጊዜ ይመጣል። ለጥቅም ሲሉ በሃሰት ለመመስከር ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎችን ማዋረድ፣ መናቅና ማግለል ተገቢ እና ከስነ-ምግባር አኳያ ተቀባይነት ያለው ተግባር ነው ብሎ ያምናል።

የመለስ ዜናዊ ዘረኛ አገዛዝ በሽብረተኝነት የፈጠራ ክስ በሚያንገላታቸው ወገኖቻችን ላይ በሰየመው የይስሙላ "ችሎት" ቀርበው መሃላ ፈጽመው እንዲዋሹ የሰለጠኑ ሰዎች የሚያደርጉትን ማየት በእጅጉ ያሳፍራል። ኅብረተሰባችንም ለእንዲህ ዓይነቶች ውሸታም ምስክሮች የሚሰጠው አንዳችም አዘኔታ ሊኖር አይገባም። "ተገድጄ ነው የመሰከርኩት" ማለት ተቀባይነት ያለው ምክንያት አይደለም። እነዚህ ሰዎች በመሃላ ዋሽተዋልና ስብዕናቸውን አርክሰዋል። የንጹሃን ዜጎችን ሕይወት ለገዳዮች አሳልፈው ሰጥተዋልና፤ ከገዳዮች ለይተን አናያቸውም።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ**

## ህወሃትን መደገፍ በምንም መንገድ አማራጭ አይሆንም!!!

አንዳንድ ሰዎች ህወሃትን የምንደግፈው አማራጭ ስላጣን ነው ሲሉ ይደመጣሉ። እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ የሚመጣው ነገሮችን ከሥር መሰረቱ ለማየት አቅም ከማጣት ብቻ ሳይሆን የራስን ችሎታና እውቀት ፈልጎ ካለማግኘትም ጭምር የሚፈጠር እምነት ነው።

ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ የተባለው ዘረኛና ዘራፊ ድርጅት ኢትዮጵያዊያንን አማራጭ አሳጥቶና አጎሳቁሎ እርሱ ብቻ ደልቶት እየኖረ ነው።በእነዚህ ዘረኞችና ዘራፊዎች እጅ ያለች ኢትዮጵያ ፍትህ አጥታ፤ ህግ ዜጎችን ለማጥቂያ ጥሩ መሳሪያ ሆኖ፤ ጥቂቱ ብዙሃኑን ተጭኖ ብዙሃኑም ጥቂቶቹን ተሸክሞ ስቃይና መከራው በዝቶ እየኖረ ባለበት በዚህ ዘመን አማራጭ ስላጣው ዘረኝነትንና ዝርፊያን እደግፋለው ማለት አሳፋሪ ነው።

በመለስ ዜናዊና ቡድኑ እምነት መሰረት "ዜጎች ሁሉ እኩል ናቸው ነገር ግን ጥቂት ዜጎች ይበልጥ እኩል ናቸው" የሚል እንስሳዊ መርህ ይዘው ዜጎችን በመከፋፈል ተግባር ላይ ተጠምደው ብዙ ዓመታትን አስቆጥረዋል። አንዱን የህዝብ ክፍል አንተ እኮ "ወርቅ" ነህ ሲሉት ሌላውን ደግሞ "አህያ" እያሉ መሳደባቸው የሚታወቁበት መልካቸው ነው።አንዱን የህዝብ ክፍል አንስተው የሌላው ጠላት አድርገው ሲሰብኩ ትንሽም የሂሊና ወቀሳ የማይሰማቸው መሆኑን ማየት የሚችል አይቷል መስማት የሚችልም ሰምቷል። "የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላት አማራ ነው" ብሎ ጽፎና መመሪያ አድርጎ የሚሰራ የክፉዎች ቡድን መሆኑንም ዘወትር ማስታወስ የሚገባን መሰረታዊ ነገር ነው። አንዱ የህዝብ ክፍል በሌላው እንዲጠላና እንዲራራቅ ለማድረግ የህዝቡን ግማሽ ጎን በቦንብ ለማስደብደብ፤ ገድሎ ገደል እንዲጨመሩ ለማድረግ ወደ ኋላ አለማለታቸውን አይተናል ሰምተናልም። እንዲህ ዓይነቱን ነፍሰ ገዳይ ቡድን አማራጭ ስላጣው እደግፋለው ማለት ፈጽሞ አሳፋሪ ነው።

መለስ ዜናዊ በዙሪያው ብዙ ሆድ አደሮችን ሰብስቧል። እነዚህ ሆዳቸው እስከሞላ ድረስ አገሪቷ ከገጸ ምድር ብትጠፋ ግድየላቸውም። ህዝብ ርስ በርሱ ቢተላለቅ እነርሱን የሚያስደነግጣቸው አይደለም። እንዲያውም እንዲያ ያለ ነገር እንዲፈጠር በዘረኝነት ልክፍት የተያዘው መለስ ዜናዊ የሚያዛቸውን ለመፈጸም የሚሽቀዳደሙ ናቸው። አእምሮአቸው ከሆዳቸው ዘሎ ማሰብ ባለመቻሉም አገሪቷ ለምና ያገኘችውን ገንዘብ እየዘረፉ በውጭ አገራት ባንክ ውስጥ ይደብቃሉ። ልጆቻቸውንና ዘመዶቻቸውንም እንደላቀው በውጭ አገራት ያስተምራሉ ያኖራሉ። የቀደሙ ዜጎች ያኖሩትን ድንበር እያፋረሱ የአባቶቻችን የደም መሬት የሆነውን ለባእዳን ይሰጣሉ። ይሸጣሉ። እንዲህ የሚያደርገውን ቡድን አማራጭ ስላጣሁ እደግፋለው ማለት ካሳፋሪነትም በላይ ነው።

የአገሪቷን ፍትህ ሥርዓት አዋርደው የግል መጠቀሚያቸው አድርገውታል። ዛሬ በአገራችን የህግ የበላይነት በመለስ ዜናዊ ስሜት ተተክቷል።የዚህ ሰው ስሜት ህግ በሆነበት አገር "እኔ ሰው ነኝ" ማለት አሸባሪነት ሆኗል። "የመናገር ነጻነት ይከበር" ማለት በአገር ክዳት ወንጀል የሚያስከሥሥ ሁኗል። "የሰብዓዊ መብት ይከበር" ማለት በስቅላት የሚያስቀጣ ወንጀል ሁኗል። ሰላማዊ ሰልፍ ለማድረግ ማሰብና መጠየቅ መንግስትን በአመጽ ለመገልበጥ የሚደረግ ተግባር ነው ተብሏል። ኢትዮጵያ ውስጥ በሰላም ገብቶ ለመውጣት ስለመለስ ዜናዊ ቅንድብ ማማር መዝፈን እና የወያኔን ልማታዊ መንግሥትነት ማወደስ አስፈላጊ የሆነበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። እንዲህ የፍትሁን ስርዓት አዋርደው የግል መጠቀሚያ ያደረጉ ኃይሎችን አማራጭ ስላጣሁ እደግፋለሁ ማለት ነውር ነው።

በአገራችን ውስጥ በተጨባጭ የሚታየው ጥቂት የትግራይ ገዥ ጉጅሌዎች ብዙሃኑን ተጭነው ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊም እነርሱን ተሸክሞ ስቃይና መከራው በዝቶ መኖሩ ነው። እነዚህ ጥቂቶች ለንጽፅር ተብሎ በአንድ ወቅት አደባባይ በወጣው መረጃ በአንድ መንግስታዊ ተቋም ማለትም በአገሪቷ መከላከያ ውስጥ ካሉ ስልሳ አንድ የጦር ጄኔራሎች ሃምሳ ሰባቱን የሚቆጣጠሩ ሆኖ የመገኘቱ ምስጢር ብዙሃኑን ረግጠው ለመኖር ካላቸው ቅዥት የተነሳ ነው። በዚህ ብቻ አያበቃም የአገሪቷ የድህንነት መስሪያ ቤት ሙሉ በሙሉ በአንድ አካባቢ ልጆች ቁጥጥር ስር መውደቁ ዜጎችን ለመጫንና ለማሰቃየት የተመቸ መንገድ ፈጥሮላቸዋል። በእነዚህ ጦር አዛዦችና የድህነቱ መሥሪያ ቤት ሹመኞች አማካኝነ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ለስደት ተዳርገዋል። በየቦታው ተገለው የተጣሉትን ቤቱ ይቁጠራቸው። የተለያየ የፈጠራ ወንጀል ታፔላ ተለጥፎባቸውና የሃሰት ምስክር ተዘጋጅቶ ወህኒ የተወረወሩ ዜጎችን ቆጥረን አንዘልቀውም። መለስ ዜንዊ በድሆች ስም ለምኖ ያመጣውን ገንዘብ የገዛ አገሩን ዜጋ ለማስለል በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ውስጥ ላሰማራቸው ሰላዮች ሲያውል ቅንጣት ታክል ቅሬታ አይሰማውም። ለመለስ ዜናዊ ከስልጣኑ የሚበልጥበት ምንም ነገር የለም። የህዝቡ መራብና መቸገር ለእርሱ ተረት ተረት ነው። እንዲህ ዓይነቱን የሚያይ ዓይን የሚሰማ ጆሮም የለውም። "Animal farm" በተባለ መጽሃፍ ውስጥ ከዋነኞቹ ተዋኒያን መካከል መለስ ዜናዊ ናፖሊዮን የተባለውን ገጸ ባህሪይ የመስላል። እንዲህ ዓይነቱን እኩይ ግለሰብ አማራጭ ስላጣሁ እደግፋለው ማለት "ሁለት እግሮች መጥፎ አራት እግሮች ሁሉ ጥሩ"እያሉ ከሚያላዝኑ በጎች ጋር መሳ ለመሳ የሚያቆም አባባል ነው።

በመጨረሻም የሰው ልጆች ምርጫ አጥተው አያውቁም። ምርጭ ሞልቷል።ምርጫ ያሳጣንን ሃይል ምርጫ ስለጠፋ ከመደገፍ ይልቅ ይህንኑ ቡድን ወይም ሃይል ለማስወገድ መታገል የተሻለ ምርጫ ነው። እነ መለስ ዜናዊ ካሁን በኋላ ተመክረው የሚመለሱ አይደሉም። የአንድ ትውልድ እድሜ ያክል የኖሩበትን ልማድ ሲፈጽሙ የኖሩትን ዝርፊያ፤ ውሸት፤ ጭካኔ፤ ግድያ እና የሰው ልጆችን ማሰቃየት ይተዋሉ ማለት አይቻልም። መለስ ዜናዊንና ቡድኑን መደገፍ ለራሱ ክብር ከሚሰጥ ዜጋ የሚጠበቅ ተግባር አይደለም።ለራሱ ስብእና ክብር የሚሰጥ ዜጋ ምርጫ ያሳጡ ሃይሎችን በሚችለው ሁሉ ይታገላል እንጂ ምርጫ ስላጣሁ እደግፋቸዋለሁ አይልም።

የተከበራችሁ ወገኖቻችን መለስ ዜናዊንና ቡድኑን መደገፍ በምንም መልኩ ምርጫ አይሆንም። በዚህ ወቅት ዘረኝነትንና ዝርፊያን በቃ ማለት በእጅጉ የተሻለ ምርጫ ነው። ከልዩነቶቻችን ይልቅ አንድነቶቻችን ላይ እናተኩር። ተስፋ ከመቁረጥ ይልቅ ከነመለስ ዜናዊ ዘረኛና ዘራፊ ቡድን በኋላ ስለምትመሰረተው ኢትዮጵያ አጥብቀን እናስብ። ከደመናው ባሻገር የነጻነት ጎህ ሲቀድ ለማየት የአእምሯችንን ልቀት አንወስን። እነመለስ ዜናዊ "እኛ ከሄድን ኢትዮጵያ ትበታተናለች" የሚሉትን ሟርት "እኔ እያለሁ አገሬ አትበተንም" በሚል ከራስ መተማመን በሚመነጭ ውሳኔ እንንገራቸው። ኢትዮጵያ አገራችን ለሉአላዊነቷና ለዘላቂ ጥቅሟ ከመለስና ግብረአበሮቹ በላይ ጠላት እንደሌላት እናሳውቃቸው። የእነመለስ ጥረት እራሳቸው በፈጠሩት የእርስ በርስ ጦርነት ስጋት ውስጥ ወድቀን የነርሱን ሰላም አስከባሪነት በመሻት እስከወዲያኛው እንድንገዛላቸው ነውና ይህንን ምኞታቸውን እንደ ጠዋት ጤዛ ማርገፍ፤ እንደ ጉም ብን ብሎ እንዲበን ማድረግ ለፍትህ፤ ለእኩልነትና ለዲሞክራሲ የምንታገል ሃይሎች ሁሉ ሃላፊነት ነው።

**ኢትዮጵያችን ለዘላለም ትኑር !!!!**

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የሠራዊቱን የብሔር ተዋጽኦ ለማመጣጠን የምልመላ መስፈርቶች ዝቅ እንዲል . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

በመከላኪያ ሠራዊት ውስጥ ሊተገበር የታቀደውን የብሄረሰብ ተዋጽኦ አስመልክቶ ከትናትና ወዲያ ማክሰኞ በወያኔ ፓርላማ ፊት ቀርቦ ያስረዳው የይስሙላ ምንስትር ሲራጅ እንደተናገረው፤ በመከላኪያ ውስጥ ዝቅተኛ ተሳትፎ አላቸው በተባሉት ክልሎች በምልመላ ወቅት እስከ ዞን ድረስ በመውረድ ወጣቱ ስለተቋሙ ግዳጅ እንዲረዳና ስለአገር መከላከል ግንዛቤ እንዲኖረው ከማድረግ ባሻገር፣ በሌሎች ክልሎች የሚጠየቀው የአሥረኛ ክፍል ትምህረት ማጠናቀቅ መመዘኛ አይሆንም ከመባል አልፎ ለነዚህ ክልሎች ተመልማዮች አምስተኛ ክፍል መድረስ በቂ ነው ተብሎአል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በርካታ ታዛቢዎችን ያሳቀው የወያኔ ድራማ በመከላኪያ ውስጥ ወደ ወታደራዊ መኮንንነት ማዕረግ ለመግባት በሚደረገው የሳይኮሜትሪክ ምዘና መነሻ 65 ከመቶ ነጥብ የነበረው ወደ 45 ከመቶ ዝቅ እንዲል ተደርጎአል መባሉ ነው። ከ10ኛ ክፍል በላይ ትምህረት ደረጃ እንደሌለው በግልጽ የሚታወቅ ሰው የአገሪቱ የመጀመሪያው ሙሉ ጄነራል በሆነበትና ከታች ከመቶአለቅነት እስከ ጀነራልነት ያሉት ማዕረጎች ላይ የተኮለኮሉት ሁሉ በተመሳሳይ የትምህረት ደረጃ ላይ ያሉ የአንድ መንደር ተወላጆች በሆኑበት አገር ለአዳዲሶቹ የወደፊት ሰልጣኝ መኮንኖች መስፈርት መበጀቱና ፈተናውን የትኛው መኮንን ሊያዘጋጀው እንደሚችል አለመታወቁ ወያኔ እያወራው ያለው የጥገና ለውጥ አይናችሁን ሸፍኑና ላሞኛችሁ የሚለው የተለመደው ቅጥፈት አካል ነው።

ለወያኔ ተወካዮች ምክር ቤት በቀረበው የመከላኪያ ሪፖርት ሌላው አስቂኝ እነመለስ መተካካት በሚሉት አሰራር በ2003/04 በጀት ዓመት በሦስት ዙር ቁጥራቸው 561 የሚሆኑ ከፍተኛ አመራሮች በመተካካት ሒደቱ እንዲቀነሱ ታቅዶ፣ በሁለት ዙር 13 ጄኔራሎች፣ 303 ኮሎኔሎችና ሌተና ኮሎኔሎች በድምሩ 316 አመራሮች ተተክተዋል መባሉ ነው።

በወያኔ የመተካካት ፖሊሲ ተቀንሰዋል የተባሉት 13 ጄነራሎችና የተቀሩት ባለማዕረጎች አገዛዙ በጥብቅ ሊቆጣጠራቸው ወደሚፈልገው ሌሎች የሲቪል መስሪያቤቶች ተዛውረው በመከላኪያ ውስጥ ከነበራቸው ጥቅማጥቅሞች የበለጠ እንዲያጋብሱ እየተደረገ መሆኑን እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እንደሚያውቅ የወያኔ ገዢዎች የሚገነዘቡት አይመስልም።

ይህ በዚህ እንዳለ በመከላኪያ ውስጥ ያለውን ዘረኛ አወቃቀር በመቃወም በርካታ ወታደሮችና የበታች መኮንኖች ከሥራገበታቸው እየኮበለሉ እንደሆነ የግንቦት 7 ንቅናቄ መረጃ ምንጮች ገለጹ። በመከላኪያ ሠራውቱ ውስጥ ያለው ዘረኝነት አሁንም አልቀነሰም የሚሉ ምንጮች እንደምናገሩት ለምሳሌ በሰሜን ዕዝ ስር ካሉት 9 ክፍለጦሮች ውስጥ በሻምበል መሃመድ ከሚመራው 24ኛ ክፍለጦርና በአዛዥ ከፍያለው ከሚመራው 25ኛ ክፍለጦር በስተቀር የ7ቱም ክፈለ ጦር አዛዦች ትግሪኛ ተናጋሪዎች ናቸው። ትግሪኛ ተናጋሪ ያልሆኑት አዛዦች ይመሩታል የተባሉት የ24ኛና 25ኛ ክፍለጦርም ቢሆኑ የዘመቻ መኮንኑና የሎጀስቲክ ሃላፊነት ቦታዎች ላይ ያሉት እነርሱ ናቸው።

በዚህም የተነሳ እያንዳንዱ የጦር አባል ደስተኛ አይደለም የሚሉ ምንጮች ጦሩ ውስጥ ያለው ክፍፍልና በሥር ዓቱ ላይ ያለው ጥላቻ በሲቪሉ ህበረተሰብ ውስጥ ካለው የከፋ ነው ። የጦሩ አባላት በአገዛዙ ላይ ያላቸው ጥላቻ እንዲጨምር እያደረገ ያለው የሰራዊቱ አባላትን በፍርሃት ለማሽመድመድ ተብሎ በጊዜው በሚደረገው ግምገማ ላይ ሰዎች ለቀልድና ለጫወታ የተናገሩት ሳይቀር ወደፖለቲካ እየተመነዘረ የሚቀርበው ሂስ እንደሆነ የደረሰን መረጃ አመልክቶአል። እርስ በርስ መተማመን እንዳይቻል በተደርገበት የወያኔ ሠራዊት ውስጥ ማንም አባል እከሌ ይቀርበኛል ብሎ የሆዱን አውጥቶ ለማንም አንደማያጫውትና ይህ እራሱን የቻለ ማህበራዊ ቀውስ ስለፈጠረ ብዙዎች የአገልግሎት ጊዜያቸውን ጨረሰው የሚሰናበቱበትን ቀን በጉጉት የሚጠብቁ ናቸው። (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ሁለቱ የስዊድን ጋዜጠኞች በወያኔ ፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ብይን ተላለፈባቸው

ጋዜጠኛ ማርቲን ሽብዬ እና ጆሀን ፐርሰን በሶማሌ ክልል ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ያለው የስዊድን ነዳጅ ፈላጊ ኩባንያ፤ እነሱ እንዳሉት፡-በአካባቢው ነዋሪዎችና በሰራተኞች ላይ የሰብዓዊ መብት ጥሰት መፈጸምና አለመፈፀሙን ለማጣራት"፤ ከኦጋዴ ነፃ አውጭ ግንባር ተዋጊዎች ጋር በመሆን ድንበር አሳስብረው ወደ ክልሉ ለመግባት ሲሞክሩ በኢትዮጵያ ወታደሮች ቆስለው የተያዙት፤ ከስድስት ወር በፊት ነው።

ጋዜጠኞቹ በቁጥጥር ስር በዋሉ ማግስት ሽብርተኝነትን ጨምሮ ተያያዥነት ያላቸው ሌሎች ሁለት ክሶች የተመሰረተባቸው ቢሆንም፤ ጉዳያቸውን እየተመለከተ ያለው ፍርድ ቤት የሽብርተኝነት ክሱን ውድቅ በማድረግ፡- "ሽብርተኝነትን በመርዳት" እና "ያለ ፈቃድ የአንድን ሉዓላዊ አገር ድንበር መጣስ" በሚሉት ሁለት ክሶች እንዲከላከሉ ውሳኔ መስጠቱ ይታወሳል።

ይሁንና በፍርድ ቤቱ የክርክር ሂደት ጋዜጠኞቹ ላይ ከቀረቡት ማስረጃዎች መካከል አብዛኞቹ ጋዜጠኞቹ ለፖሊስ "ሰጥተዋቸዋል" ከተባለው ቃል ላይ የተወሰዱ ቢሆኑም፤ ፖሊስ ካቀረባቸው ከነዚህ ማስረጃዎች ውስጥ አንዳቸውም እውነት እንዳልሆኑ ራሳቸው ጋዜጠኞቹ ለፍርድ ቤቱ አስረድተዋል።

"ሽብርተኝነትና የሽብርተኛ ተባባሪ" የሚለው ክስ እንደማይመለከታቸው የገለጹት ጋዜጠኞችም፤ ያለፈቃድ ወደ ኢትዮጵያ ድንበር መግባታቸውን በማመን ይቅርታ መጠየቃቸውም አይዘነጋም።

ይሁንና ከምርመራ ጋዜጠኝነት ሙያዊ ግዴታ አንፃር ወደ ሌሎች አገሮችም በተመሳሳይ መንገድ መግባታቸውን የአገሮቹን ስም በመጥቀስ ያብራሩት ጋዜጠኞቹ፤ ወደ ኢትዮጵያም የገቡትም ሙያዊ ግዳጃቸውን ለመወጣት እንጂ ለሌላ ተልዕኮ እንዳልሆነ አስረድተዋል።

ከዚህም ባሻገር ተከሳሾቹ ሽብርተኛም ሆነ የሽብርተኞች ተባባሪ ላለመሆናቸው፤ ከመቶ የሚበልጡ ጋዜጠኞች ለመመስከር ዝግጁ መሆናቸውን ያሳወቁ ሲሆን፤ ፍርድ ቤቱ ግን በቂ ነው በማለት የ20 ምስክሮችን ቃል ሰምቷል።

ሁሉም ጋዜጠኞች በሰጡት የምስክርነት ቃል የምርመራ ዘገባ( ኢንቨስቲጌቲቭ ሪፖርት) በሚሰሩበት ጊዜ ጋዜጠኞች ከዚህም በላይ ህይወታቸው አደጋ ላይ እስኪወድቅ ድረስ ብዙ መስዋዕትነት በሚያስከፍሉ ስፍራዎች ላይ በመገኘት እንደሚዘግቡ በስፋት በማብራራት፤ማርቲን ሽብዬ እና ጆሀን ፐርሰንም አሁን ላጋጠማቸው ፈተና የተዳረጉት ለሙያቸው ካላቸው ፍቅር በመነሳት እንጂ ሌላ ፍላጎትና ዓለማ ስላላቸው እንዳልሆነ አስረድተዋል።

ቀጥታ ከላይ እንደወረደለት ሞትና ዕድሜ ልክ መፍረድ የለመደው በ ሽምሱ ሲርጋጋ የሚመራው ፍርድ ቤት ግን፤ ስለ ጋዜጠኞቹ ንፅህና ከበቂ በላይ ምስክሮችና ማስረጃዎች ቢቀርቡለትም፡- ጋዜጠኞቹ ከስዊድን ወደ ለንደን በመሄድ በኦጋዴ ነፃ አውጭ ግንባር መሪዎች የጉዞ አመቻችነት በኬንያ አድርገው ወደ ኢትዮጵያ መግባታቸውን በመጥቀስና፤ በምርመራ ዘገባ ስም የአገርን ድንበር እንደጣሱና ከ አሸባሪ ድርጅት እንደተባበሩ በማውሳት - የ አንድን ሉአላዊ አገር ድንበር በህገ ወጥ መንገድ መጣስ እና የሽብርተኛ ድርጅት ተባባሪ በሚሉት ሁለት ክሶች የጥፋተኝነት ብይን አሳልፎባቸዋል።

አየር እንዳትተነፍሱ የሚል አንቀጽ ብቻ በቀረው በኢትዮጵያ የሽብርተኝነት ህግ መሰረት ጋዜጠኞቹ ከ15 ዓመት እስከ ዕድሜ ልክ የሚደርስ እስራት ይጠብቃቸዋል።

በኢትዮጵያ የስዊድን አምባሳደር ፍሬድሪክ ሬይንፌልድት ጋዜጠኞቹ ጥፋት ስለሌባቸው በነፃ ይሰናበታሉ የሚል ተስፋ እንዳላቸው መግለፃቸውን ተከትሎ-ስማቸውን መጥቀስ ያልፈለጉ አንድ የተቃዋሚ ፓርቲ መሪ ጉዳዩን አስመልክቶ ባለፈው ሳምንት ለ ኢሳት በሰጡት አስተያዬት፤ ፍርድ ቤቱ በጋዜጠኞቹ ላይ ከቀረቡት ሶስት ክሶች ሁለቱን ከመቀበሉ አኳያ በሚተላለፈው ብይን ላይ ተስፋ እንደሌላቸው መናገራቸው ይታወሳል።

በተለይ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያና በስዊድን መካከል ያለው ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እየሻከረ መምጣቱ በጋዜጠኞቹ ላይ በሚተላለፈው ብይን ላይ የራሱ ተጽዕኖ እንደሚኖረው የጠቆሙት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪው፤ ይህም የሁለቱን አገሮች ግንኙነት ይበልጥ ቫኢያበላሸው ይመጣል የሚል ስጋት እንዳላቸው ተናግረዋል።

በጋዜጠኞቹ ላይ የተላለፈውን የጥፋተኝነት ብይን ተከትሎ፤ ዓለማቀፍ የጋዜጠኞች መብት ተንከባካቢ ድርጅቶች ተቃውሟቸውን እያሰሙ ይገኛሉ።

## በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በወያኔ የግፍ አገዛዝ ተማሮ በራሱ ላይ ነዳጅ አርከፍክፎ በሎከሰው እሳት ለህልፈት የበቃውን ወጣት የኔሰው ገብሬን መዘከር እንደቀጠሉ ነው

በአገራችን ውስጥ የሰፈነውን ኢፍትሃዊነትና የግፍ አገዛዝ በመቃወም የዞንና የወረዳ አስተዳዳሪዎች ከተሰበሰቡበት አዳራሽ ደጃፍ ላይ በአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ አሰቃቂ አሟሟት ህይወቱን መስዋዕት ያደረገውን መምህር የነሰው ገብሬን የሚዘክር የተለያዩ ስብሰባዎች በሰሜን አሜሪካና በአውሮፓ እየተካሄደ መሆኑን ለዝግጅት ክፍላችን የደረሱኡ ዘገባዎች አመለከቱ።

በቅርቡ በሰሜን አሜሪካ የተለያዩ ክፍለግዛቶች መዘከር የተጀመረው የመምህር የኔሰው ገብሬ መስዋዕትነት ባለፈው ቅዳሜ ና እሁድ (ታህሳስ 7 ና 8/2004 ዓ.ም) በሎሳንጀለስና በኒዘርላንድስ መካሄዱን የሚገልጹ ዘገባዎች፡ ያመለክታሉ በሆላንድ ርዕሰ ከተማ በአምስተርዳም በተደረገው ስነሥርዓት ላይ በከተማው የሚኖሩ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበራት ወኪሎች ንግግር እንዳደረጉም ይገልጻል።

በሆላንድ በኢትዮጵያ ኮሚኒቲ አስተባባሪነት በተካሄደው በዚህ ሥነሥርዓት ላይ በሆላንድ የሲቪክ ማህበራት ተወካይ የሆኑት አቶ ቦጋለ ካሳየ እንደተናገሩት፤ የመምህር የኔሰው ገብሬ መስዋዕትነት ፍትህና እኩልነት ለሚናፍቀው ለኛ ትውልድ ከፍተኛ የሆነ እዳ ጥሎ አልፎአል። ይህንን የተጣለብንን እዳ ለመወጣት ደግሞ "ከራሳችን ጋር በመታረቅ፣ ጭቆናን አምርረን ልንቃወምና ወያኔ በትናንንሽ ጥቅማጥቅሞች እየደለለ ሊከፋፍለን የሚያደርገውን ጥረት በጋራ መክተን አድሎአዊነትን፤ ጭቆናንና ግፍን በመዋጋት በአገራችን ስላምና ብልጽግና ለማምጣት ሁላችንም በጋራ ልንቆም ይገባል ስለዚህም ሁላችንም ለፍትህና ለእኩልነት የሚደረገውን ትግል የማገዝ ሃላፊነታችንን በመወጣት መምህር የኔሰው የተሰዋለትን አላማ ከግብ ማደረስ አለብን" ብለዋል።

በመቀጠልም የተናገሩት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት አመራር አባል የሆኑት ዶ/ር አረጋዊ በርሄ "የኔሰው የፈጸመው ገድል ከእነ አጼ ቴዎድሮስና አቡነ ጴጥሮስ የሚተናነስ አለመሆኑን ገልጠው፣ በየኔሰው ሞት የሽብረተኛው አምባገነን አገዛዝ ትክክለኛ ማንነት ተጋልጦአል ካሉ ቦሃላ የኔሰው በህይወቱ በከፈለው መስዋትነት አገራችን ያለቹበትን አስከፊ ሁኔታ ተገንዝበን አሁን ከገባንበት ትርምስ ለመውጣትና የኔሰው ጥሎልን ያለፈውን ጥሪ ለመመለስ በሰከነ መንገድ መወያየት፣ መደጋገፍ፣ የተዘበራረቁና የሚተራመሱ ሀይሎች ቋሚ መፍትሄ መፈለግ ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ወያኔ በግንቦት 7 አመራር አባልነትና የቤልጂዬም ተወካይነት በቅርቡ ክስ የመሰረተባቸው አቶ መስፍን አማን በበኩላቸው ሙስና፣ ዘረኝነት፣ አድልዋና ራስ ወዳድነት በሰፈነባት ኢትዮጵያ ፣ የኔሰው የከፈለው መስዋትነት ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ የየኔሰው ጥያቄ ተመለሰ የሚባለው አሁን በስልጣን ላይ ያለውን ዘረኛ መንግስት ታግለን ስናስወግድ ብቻ ነው በማለት ገልጠዋል። አቶ መስፍን አከለውም የቱኒዚያው አምባገነን መሪ የነበሩትን የቤን አሊን አስተዳደር በመቃወም በራሱ ላይ ያንን አይነት እርምጃ የወሰደውን ሞሃመድ ቡአዚዝ ራሱን ባቀጣለበት ጊዜ የቀድሞ የአገሪቱ መሪ ቤን አሊን ሆስፒታል ድረስ ሂደው ሲጎበኙት የእኛዎቹ ግን ስሙን ለማጥፋት መሽቀዳደማቸው፣ የምንታገለው መንግስት ምን ያክል እኩይ እንደሆነ ያሳያል ብለዋል።

የየኔሰው ገብሬን መስዋዕትነት ለመዘከር ሆላንድ ላይ በተዘጋጀው በዚህ ሥነሥርዓት ላይ የተለያዩ ሰዎች ስለወያኔ አስከፊነትና በአገራችን ስለሰፈነው ኢፍትሃዊነት በመዘርዘር ሁሉም አምርሮ መነሳት እንዳለበትና ለነጻነት የሚካሄደውን ትግል ማጠናከር እንደሚኖርበት ጥሪ አስተላለፈዋል።

## የሠራዊቱን የብሔር ተዋጽኦ ለማመጣጠን . . . (ከገፅ 3 የዞረ)

በሰራዊቱ አለመረጋጋትና ደስተኛ አለመሆን የተደናገጡ የወያኔ ሹሞች ካለፈው ነሃሰ ጀምሮ ልዩ የደመወዝ ጭማሪ ያደረጉ ቢሆንም ያመጣው መሰረታዊ ለውጥ እንደሌለ ይነገራል። በአዲሱ የደመወዝ ጭማሪ የአንድ ተራ ወታደር ደመወዝ በወር 800 ስምንት መቶ ብር ሲሆን የአንድ መቶ አለቃ ደመወዝ በወር 1860 አንድ ሺ ስምንት መቶ ስልሳ ብር ደርሶአል። ከመቶአለቅነት ማዕረግ በላይ ያሉት አብዛኞቹ የህወሃት አባላት በመሆናቸው እነርሱን ለመጥቀም ሲባል የወንበር አበል በሚል ሰበብ በወር 200 ብር ሲከፈል እንደነበረ የገለጹት ምንጮች የመቀመጫ አበል ተብሎ የሚከፈለው ገንዘብ በወታደሩ መካከል ባስከተለው ተቃውሞ ምክንያት እንደተቋረጠ ገልጸዋል።

በወያኔ ጦር ውስጥ ያለው የዘር ስብጥር ተቃውሞ ያስነሳው ከ95 በመቶ በላይ የአዛዥነት ቦታ ላይ ተመድበው የሚገኙት ከአንድ ብሄረሰብ ማለትም ከትግራይ መሆኑ ሆኖ እያለ ወያኔ የዘረን ተዋጾ ለማድረግ ዕቅድ እንዳለው እየነገረን ያለው በተራ ወታደርነት ያለውን ዘርፍ ነው። እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እምነት በተራ ወታደርነት ደረጃ ያለው የብሄረሰብ አስተዋጾ በመስፈርትነት መቀመጡ ምንም ትርጉም የለውም። መጻፍና ማንበብን ለመጀመሪያ ጊዜ አዲስ አበባ ከገቡ ቦኋላ የተማሩት የህወሃት የቀድሞ ታጋዮች ከሻለቃ ማዕረግ እስከ ጀነራልነት ተሹመው ባለበት ሁኔታ ለተራ ወታደር ምልመላ የ10 ኛ ክፍል ትምህረት ወይም ከዚያ በታች ያለው በመስፈርትነት መቀመጡ ወያኔ እየተከሰሰበት ያለውን ዘረኝነት ሊያሻሽል አይችልም በብዙዎች እምነት።

## የህወሀት ጄኔራሎችና ኩባንያቸው ኢፈርት በጦር . . . (ከገፅ 1 የዞረ)

መሆኑን ገልጾአል። መስፍን ኢንጂነሪንግ የወዳደቁ የግብርና ብረታ ብረቶችን፣ ከፈራረሱ ሆስፒታሎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የሀይል ማመንጫዎች የተገኙ የአርማታ ብረቶች፣ የወዳደቁ መኪኖች፣ የከባድ ጦር መሳሪዎች የተሰሩባቸውን ብረቶች፣ እንዲሁም የተለያዩ የእንጨት ውጤቶችን የህወሀት እህት ኩባንያ በሆነው ትራንስ ኢትዮጵያ እየጫነ በመውሰድ ላይ ነው ያለው ኢሳት መስፍን ኢንጂነሪንግ ለፑንትላንድ እና ለጁባ የጦር አለቆች ክፍያ መፈጸምና አለመፈጸሙ እንዳልታወቀ ገልጾአል።

ይሁን እንጅ ኩባንያው ከዚህ ቀደም ከዩክሬን እና ከቱርክ ያስመጣ የነበረውን የብረታ ብረት አቅርቦት በመቀነስ፣ ያለቀረጥ ከሁለቱ አገሮች እያስገባ ያለው ብረታ ብረት የተለያዩ ድጎማዎች የሚደረጉለትን ኩባንያ እጅግ ትርፋማ ሊያደርገው ይችላል ብሎአል።

የፑንትላንዱ መሪ አብዱረህማን ሙሀመድ ፋሩሌ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተደጋጋሚ ወደ አዲስ አበባ እንደሚመላለስ ኢሳት በዘገባው ገልጾ በመለስ ዜናዊ የሚመራው የወያኔ አገዛዝ በአንድ በኩል ጁባ ላንድ የራሷን አስተዳደር ለመመስረት የጀመረቺውን ትግል የማይደግፍ እየመሰለ በጎን ግን በጄነራሎች አማካይነት ለጦር መሪዎቹ ህገወጥ የጦር መሳሪያ ሺያጭ በማጧጧፍ ከፍተኛ የሆነ ገንዘብ በማጋበስ ላይ መሆኑን አጋልጦአል።


**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።



**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org